# ኧረ ምን ይሆን ሚስጢሩ

ኧረ ምን ይሆን ሚስጢሩ የችግራችን ተአምሩ
አላልቅ ያለው መዘዛችን የመከራችን ጣሩ
ውሉ እንደጠፋ ማግ ተውሰብስቦ ዕይታችን
የተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ስህተት ፈላጊ ተቺ ሆነን
ራዕይ አልባ ሆነን በደመነፍስ እየተጓዝን
እኔ ምን ሠራሁ ላገሬ ብለን ሳንጠይቅ ራሳችንን
ታሪክ ባህላችንን ኢትዮጵያዊ ወኔያችንን
እርግፍ አድርገን ረስተን ጆሮ ዳባ ልበስ ብለን
እርስ በርሳችን ተፈራርተን ተጠላልፈን
በአፍ አንድነት በክህደት ሽፍጥ ተወጥሮ ውስጣችን
ተሰባስበን እንዳናብር እንዳንሆን ሀይል
እንዳናቅድ እንዳንቀይስ ሁለገብ የጋራ ትግል
የአንድነት እትብታችን እንዲመረዝ እንዲበጠስ
ኧረ ምን ይሆን ሚስጢሩ የችግራችን ሴራ ጥንስስ
እስኪ መለስ ብለን እንመርምር የኋላ ታሪካችንን
ፍንጭ የሚሰጥ ገላጭ ነገር ፈዋሽ ቢኖር ላበሳችን
ተዘርዝሮ ለማያልቀው ለአኩሪ ታሪካችን
ትልቁ ቁልፍ ተአምረኛው የነበረው በውስጣችን
በእምነት የታነፀው አንድነትና ፍቅራችን
የክሩሴድ ጦርነት ሳያምሰን ሳይለያየን
የባእዳን ወረራ የከፋፍለህ ግዛው ዘዴ ሳይበትነን ሳይበግረን
የኢትዮጵያዊነታችንን መግለጫ የአንድነት እትብታችንን
ለማደፍረስ ለመመረዝ ለማመንመን ለመበጠስ
ይኖር ይሆን የታቀደ የተሸረበ ሴራ ጥንስስ
የጂኦ ታሪካችን ጦስ የአበሳችን መዘዝ
የቀይ ባህር ክብረ ወሰን የአባይ ፏፏቴ ወንዝ
እንዳንዋደድ እንዳንግባባ እንድንፈጥር ልዩነት
ካብራካችን የወጣውን የሰለጠነውን በሌብነት
ከሀዲውን ሆዳሙን ሱስ የያዘውን የባንዳነት
በቁሳቁሱ ጥቅም በፔትሮዶላር በመሸመት
ተሸርቦ ከሆነ የችግራችን መተት
ወደመፍትሄው የሚመራን እስኪ እናስብ እልባት
የአባቶቻችንን ብሂል አውስተን ተመርኩዘን
ማን ያርዳ የቀበረ ማን ያውራ የነበረን ለመረጃ ያህል ጠቅሰን
በምሳሌነት ጠቅስን የሚበጅ ጉዳይ ነው ብለን
እስኪ እናዋየው እናዳምጠው እንጠይቀው የምሩን
የምየን ልጅ ጀግናውን ደፋሩን ኢህአፓውን
የአስቸጋሪ ውጣ ውረድ የረጅም ትግል ባለቤቱን
የሥልጣን ሱስ ያልነካካው ለሰፊው ሕዝብ ታጋዩን
አትንኩኝ ባይ የአባቱ ልጅ አልሞት ባይ ተጋዳዩን
ለማስፈን ለመተግበር ዲሞክራሲና ፍትሕን

እስኪ እንመርምር እናስተውል ልብ ብለን ከእውነት
ወያኔዎች ከሀዲዎች ኢህአፓን ለምን ጠሉት ለምን ፈሩት
ለምንስ ባዕዳኖች እገዛቸውን ነፈጉት
በሀገር ወዳድነቱ በአርበኝነቱ እንጂ ሌላ ከቶ ምን ሊሆን
ለንዋይ አልገዛም ባይ አልሸጥም ስላለ ህሊናውን
አብጠርጥሮ ስለሚያውቅ ሸፍጣቸውን ሴራቸውን
የፖለቲካ ድራማውን የዲሞክራሲ ቀልዱን
እስኪ እንጠይቀው ይንገረን ያስተምረን ይምከረን
በረጅም ጉዞ ትግሉ የዳሰሰውን ያየውን
ሳያውቀው አይቀርምና የሴራውን ቁልፍ ሚስጥሩን
የችግራችንን ጦስ ደባ ትንግርት ጥንስሱን
ከተገኘ ክፉ ሴራ በሸፍጥ የታነጸ ክህደት
እጅ ለእጅ ተያይዘን ሆ ብለን በአንድነት
ተመካክረን ልብ ገዝተን ተማምለን በእምነት
እንድንቀይስ የጋራ ትግል የጋራ ስልት
ተደግሞብንም ከሆነ የአፍዝ የአደንግዝ ምትሀት
መርገምት ይሁን ወይም መተት ከሆነም ሌላ መዓት
የሼኪውን የቄሱን የጳጳሱን ስም በመጥራት
እንዲማለዱን ጮኸን ለገዳማትና ለአድባራት
ምትሀትን ድግምቱን የተተበተበብንን እርኩሳት
በዱአና በጸበል አርክሰንና አስወግደን
ከጨለማው ጉዞ ሆያሆዬ ከመደናበር ተላቀን
የብሩህ ተስፋ አጥቢያ ኮከብ ለኛም ቀን እንዲወጣልን
የአባቶቻችን ልጆች ታሪክ አስከባሪ እንድንሆን

# ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ከዓለማየሁ ሽመልስ
ጥር 3 ቀን 1999